# ለ ”ምርኮኛ” ደራሲ ቆንጂት ብርሃን ሕክምና
# የትብብር ጥሪ

በዕውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ታሪካዊ ልብወለድ መጽሐፍ “ምርኮኛ” ደራሲ ወ/ሮ ቆንጂት ብርሃን ለሕክምና በሰሜን አሜሪካ ትገኛለች።



ወ/ሮ ቆንጂት ብርሃን ከዛሬ 34 ዓመት በፊት ታሥራ በደረሰባት ድብደባ የተነሳ በግራ እግሯ ላይ የደረሰው ጉዳት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ደርሷል። ቆንጂት ከቀን ተቀን ከሚያሰቃያት የማያቋርጥ ህመም ባሻገር፡ የእግሯ ቅልጥም ጥንካሬ እያጣና እየሳሳ በመምጣቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበር እንደሚችል በሕክምና ባለሙያዎች ተነግሯታል። ሊደረግላት የሚገባው ሕክምና በኢትዮጵያ ባለመኖሩ ሌላ ሀገር ሄዳ መታከም ስላለባት ቆንጂት የሕክምና ዕርዳታ ለማግኘት ቤተሰቦቿንና ሥራዋን ትታ ወደ አሜሪካ መጥታለች።

ቆንጂት ለሕክምናውም ሆነ ለጊዜያዊ ኑሮ የሚረዳት በቂ ገንዘብ የላትም። በመሆኑም መጠነኛ የገንዘብ ዕርዳታ ለማሰባሰብ በWashington DC እና አካባቢው ለምትገኙ ወገኖች፡ ቅዳሜ October 22 ቀን 2011 ዓ.ም. ከምሽቱ 6፡00 p.m. ጀምሮ ቆንጂት በምትገኝበት የእራት ምሽት ተዘጋጅቷል። በእራት ምሽቱ ተካፋይ በአንድ ሰው (ከነባለቤት) $100 (አንድ መቶ ዶላር) ሲሆን ከዚያ በላይ በፈቃደኝነት ይዋጣል ብለን እንገምታለን። ከዚህ ዕርዳታ የሚገኘው ገቢ በሙሉ ለወ/ሮ ቆንጂት ይሰጣል።

ባለውለታ እህታችን ቆንጂት ብርሃን፡ <u>ህመሟ ህመማችን፤ ጭንቀቷ ጭንቀታችን፤ ስቃይዋ ስቃያችን፤</u> በመሆኑ በቻልነው አቅም ልንተባበር ይገባናል። ብርቅዬ መጽሐፏን ያነበባችሁ ሁሉ አድናቆታችሁን ለግሳችዋታል፡ በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ አካባቢ በአደረገችው የመጽሐፍ ምረቃ በዓል ላይም ያሳያችሁት ትብብር የሚዘነጋ አይደለም። እሷም ከሚገባው በላይ ተደስታበት ወደ እናት ሀገሯ ብትሄድም የደረሰባት የጤና እክል በአጭር ጊዜ ውስጥ ዳግም እንድትመለስ አስገድዷታልና በእራት ምሽቱ ላይ በመገኘት ድጋፋችሁን እንደምትሰጧት ብርቱ ዕምነት አለን። በተጨማሪም ከዚህ በፊት ተካሂዶ በነበረው የዲሲና አካባቢው የ ”ምርኮኛ” መጽሐፍ ምረቃ በዓል ላይ ለመገኘት ያልቻላችሁ ከደራሲ ቆንጂት ብርሃን ጋር በአካል ለመገናኘትና ለመወያየት ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሮአል።

በዚህ ዝግጅት ላይ መገኘት የማትችሉ በተለይ በሌሎች አካባቢዎች ነዋሪ የሆናችሁ ወገኖቻችን ሁሉ፡ ዕርዳታ ለማድረግ ከታች በተገለጹት ስልኮች በመደወል ወይም በተገለጸው አድራሻ ቼክ በመላክ ድጋፋችሁን ታደርጉ ዘንድ በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን።

የዝግጅቱ አስተባባሪ

<u>የዝግጅቱ ቦታና አድራሻ፡</u>

SUNSHINE RESTAURANT
7331 GEORGIA AVENUE, N.W.
WASHINGTON, DC 20012
(202) 248-2387

<u>ለተጨማሪ መረጃና ዕርዳታ ሰጪዎች ስልክና አድራሻ፡</u>

Berhan Dargay, Attorney at Law
1628 11th Street, N.W.
Suite 403
Washington D.C. 20001
Phone: (202)543-0665 or (202) 498-6143
E-mail: derdar202@aol.com